የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
Commercial Bank of Ethiopia

# የብድር ወለድ ምጣኔ ማሻሻያን ስለማሳወቅ

መንግስት የኢትዮጵያን የፋይናንስ ዘርፍ ተወዳዳሪ እና ሳቢ ለማድረግ ገበያ መር የሆኑ ፖሊሲዎችን እና እስትራቴጂዎችን በመቅረጽ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። ይህንንም ተከትሎ በባንክ ስራ ዘርፍ በርካታ ለውጦች እየተመዘገቡ ሲሆን፤ የባንክ ኢንዱስትሪውም በአቅርቦት እና ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የዋጋ ማሻሻያዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክም በገበያው ውስጥ ጠንካራ ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲዘልቅና በሀገራችን የኢኮኖሚ ግንባታ ላይ ያለውን የጎላ ድርሻ አጎልብቶ መዝለቅ ይችል ዘንድ ለደንበኞቹ የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋ ለማድረግ በርካታ የትራንስፎርሜሽን ስራዎችን እያከናወነ ከመሆኑም በተጨማሪ የደንበኞችን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ አዳዲስ አማራጭ የብድር አገልግሎቶችን ለማስጀመር በሂደት ላይ ይገኛል። ይሁንና ባንካችን እየተገበረው ያለው ሪፎርም አጠቃላይ የኦፕሬሽንና የአስተዳደር ወጪ እድገትን በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ ያስቻለው ቢሆንም በተለያየ ምክንያት እየተከሰተ ያለው አጠቃላይ የቁጠባ ማሰባሰቢያ ወጪ ከፍተኛ መሆንና ባንካችን ለሚሰጠው የብድር አገልግሎት የሚያስከፍለው የወለድ ምጣኔ በገበያ ላይ ከሚታየው የወለድ ምጣኔ አንጻር ሲታይ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ በባንካችን ዘላቂ ትርፋማነት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ፈጥሯል።

ስለሆነም ይህንን ለማስተካከልና ባንካችንን በፋይናንስ ዘርፉ የሚገባውን ሚና እንዲጫወት ለማስቻል ለሚሰጠው የብድር አገልግሎት ወጪውን ታሳቢ ያደረገ መጠነኛ የብድር ወለድ ምጣኔ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ነገር ግን የግብርና ዘርፍን ከማበረታታት አንፃር የወለድ ምጣኔው የተቀነሰ ሲሆን፤ የሕብረተሰቡን የመክፈል አቅም ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለኮንዶሚኒየም መኖሪያ ቤቶች ብድር የሚከፈለው የወለድ መጠን ባለበት እንዲቀጥል ተወሰኗል። በመንግስትና በግል ድርጅት ተበዳሪዎች መካከል የነበረው የምጣኔ ልዩነትም ተስተካክሏል፡፡ በዚህም መሰረት እ.ኤ.አ. ከማርች 7 ቀን 2025 ጀምሮ ባንካችን የዋጋ ማሻሻያውን ተግባራዊ እንደሚያደርግ እያስታወቅን የተደረገው የዋጋ ማሻሻያ ዝርዝር ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ተመላክቷል።

| Sr. No. | Sector | Tenure/Product | Existing Lending Rate | New Lending Rate |
|---|---|---|---|---|
| **1** | **Subsidized Loans** | | | |
| **1.1** | **Agricultural Loans** | | | |
| 1.1.1 | Agriculture (Including Fertilizer) | Short Term (Including overdraft) | 14.00% | 14.00% |
| | | Medium Term | 15.50% | 14.50% |
| | | Long Term | 16.50% | 15.50% |
| **1.2** | **Residential Condominium Loans** | | | |
| 1.2.1 | Condominium residential 40/60 | Long Term | 12.00% | 12.00% |
| 1.2.2 | Condominium residential 20/80 and 10/90 | Long Term | 12.00% | 12.00% |
| **2** | **Commercial Loans** | | | |
| **2.1** | **Non-Export** | | | |
| 2.1.1 | Term Loans | Short Term (Including overdraft) | 14.00% | 15.00% |
| | | Medium Term | 15.50% | 15.75% |
| | | Long Term | 16.50% | 16.50% |
| 2.1.2 | Condominium Commercial 40/60 | Long Term | 15.50% | 16.50% |
| 2.1.3 | Condominium Commercial 20/80 | Long Term | 15.50% | 16.50% |
| 2.1.4 | Advance on Import bills | Short Term | 17.00% | 18.00% |
| 2,1.5 | Merchandise Loan/Facility | Short Term | 15.50% | 16.5% |
| 2.1.6 | Loans to Microfinance institution | Short Term (Including overdraft) | 11.50% | 14.00% |
| | | Medium Term | 12.00% | 14.50% |
| | | Long Term | 12.50% | 15.50% |
| **2.2** | **Export** | | | |

| Sr. No. | Sector | Tenure/Product | Existing Lending Rate | New Lending Rate |
|---|---|---|---|---|
| 2.2.1 | Term Loan | Short Term (Including overdraft) | 8.50% | 12.00% |
| | | Medium Term | 10.00% | 13.00% |
| | | Long Term | 11.50% | 14.00% |
| 2.2.2 | Pre-shipment | Short Term | 8.50% | 12.00% |
| 2.2.3 | Merchandise Loans | Short Term | 8.50% | 12.00% |
| **2.3** | **Personal Loan-Employees of FCY Generating or Excepetionally Big Value Customers** | | | |
| 2.3.1 | Organizations that directly offer their FCY to CBE | Long Term | 7.00% | 11.00% |
| 2.3.2 | Organizations offering their FCY to CBE through negotiation | Long Term | 7.00% | 12.00% |
| 2.3.3 | Organization that are not open for negotiation | Long Term | 7.00% | 13.00% |
| 2.3.4 | Personal Loan-Employees of Exceptionally Big Value Customers | Long Term | 12.00% | 12.00% |
| **2.4** | **Personal Loan to Other Retail Customers** | | | |
| 2.4.1 | Mortgage Loans | Long Term | New | 14.00% |
| 2.4.2 | Vehicle loan | Long Term | New | 15.00% |
| 2.4.3 | Personal Loans | Long Term | New | 15.00% |